የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፱
አዲስ አበባ–ሰኔ ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 49
ADDIS ABABA - 3rd July, 1997

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፹፭/፲፱፻፹፱ ዓ.ም.
በግል ክፍለ ኢኮኖሚ ለተሠማሩት አነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ልማት ባንክ አማካይነት በመልሶ ማበደር የሚተላለፍ ከአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ...... ገጽ ፮፻፪

## CONTENTS

Proclamation No. 85/1997
European Investment Bank Loan Agreement for on-Lending Through the Development Bank of Ethiopia, to Small and Medium-sized Private Sector Enterprises Ratification Proclamation .......................... Page 602

### አዋጅ ቁጥር ፹፭/፲፱፻፹፱
### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በግል ክፍለ ኢኮኖሚ በፋብሪካ፣ በአግሮ ኢንዱስትሪ፣ በማዕድን፣ በቱሪዝም እና በመሳሰሉት የሥራ እንቅስቃሴዎች ለተሠማሩት አነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ልማት ባንክ አማካይነት በመልሶ ማበደር የሚተላለፍ መጠኑ ፲ ሚሊዮን (አሥር ሚሊዮን) ኢኪው የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክና በአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ መካከል እ.ኤ.አ. ዲሴምበር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ በሉግዘምበርግ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፣

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪)መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "በግል ክፍለ ኢኮኖሚ ለተሠማሩት አነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ልማት ባንክ አማካይነት በመልሶ ማበደር የሚተላለፍ፣ ከአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፹፭/፲፱፻፹፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### PROCLAMATION NO. 85/1997
### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE EUROPEAN INVESTMENT BANK

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the European Investment Bank, stipulating that the European Investment Bank provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of 10 million ECU (ten million ECU) for onlending, through the Development Bank of Ethiopia, to small and mediumsized private sector enterprises in the manufacturing, agro-industry, mining, tourism and related sectors, was signed in Luxembourg on the 18th day of December, 1996;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 3rd day of July, 1997;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the ''European Investment Bank Loan Agreement for on-Lending Through the Development Bank of Ethiopia, to Small and Medium-Sized Private Sector Enterprises Ratification Proclamation No. 85/1997.''

፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ መካከል እ.ኤ.አ. ዲሴምበር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ በሉግዘምበርግ የተፈረመው ቁጥር ፯.፩ዐ፸፫ ኢትዮ የብድር ስምምነት ነው።

፫. <u>የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲ ሚሊዮን (አሥር ሚሊዮን) ኢኪው በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ፡ ሰኔ ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት



2. *Definition*

In this Proclamaiton "Loan Agreement" means the Loan Agreement No.7.1073 ETHIO signed in Luxembourg, on the 18th day of December, 1996 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the European Investment Bank.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 10 million ECU (ten million ECU) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 3rd day of July, 1997.

Done at Addis Ababa, this 3rd day of July, 1997.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE